የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁ. ፌዋኦ/ፊ4.ፈ-06.10/3/14
ቀን 07/04/2014

ለክቡር አቶ ገለታ ስዩም

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፍትሕ ሚኒስቴር ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና

የጂንካ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ ፣ <u>የጂንካ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣</u>

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 18 ገጽ የሂሣብ መግለጫዎች ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት *

ከሠላምታ ጋር

ወርቅአፈራሁ ወንድሙ
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለጂንካ ዩኒቨርሲቲ (ከ9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 28 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እና 22 ገጽ አባሪዎች ጋር)
  <u>ጂንካ፣</u>

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

**የጂንካ ዩኒቨርሲቲ**

**የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት**

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል።

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል።

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፤</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤ ከመማር ማስተማር እና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበውን ብር 10,053,174.28 የውስጥ ገቢ እና ገቢውን ለማመንጨት ወጪ የተደረገውን ብር 10,009,460.05 ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ሲሆን በ2012 በጀት አመት ኦዲት ይህ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ያልተስተካከለ በመሆኑ የሂሳብ ሪፖርቱ ትክክለኛ ገጽታውን እንዳያሳይ አድርጓል፤
2. በበጀት ዓመቱ ለመምህራንና የተለያየ አገልግሎት ለሰጡ ሰራተኞች ከውስጥ ገቢ ክፍያ ሲፈፀም የተቀነሰው የሥራ ግብር ብር 619,180.76 ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ያልተከፈለ በመሆኑ የተከፋይና የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አለአግባብ ከፍ እንዲል አድርጓል፤
3. ዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ምረቃ ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ የቀጥታ ስርጭት ለማስተላለፍ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር ውል ገብቶ

- ጥር 15 ቀን 2013 ዓ.ም የተከናወነውን የተማሪዎችን ምረቃ ለሁለት ሰዓት ለማስተላለፍ ብር 750,000.00 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን የምረቃ ስነ ስርዓቱን ለማሰራጨት ለመጡ ጋዜጠኞች ከ15/05/2013 እስከ 24/05/2013 ለቆዩበት በሚል የ10 ቀን አበል ከብር 549.00 እስከ 724.00 በማሰብ ብር 107,090.00 ከውል ውጭ የተከፈለ መሆኑ
- ሰኔ 26/2013 ዓ.ም የተከናወነውን የተማሪዎችን ምረቃ ለሁለት ሰዓት የቀጥታ ስርጭት ለማስተላለፍ ብር 1,200,000.00 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን የምረቃ ስነ ስርዓቱን ለማሰራጨት ለመጡ ጋዜጠኞች ከቀን 12/10/2013 ጀምሮ በተቋሙ ለቆዩበት የ20 ቀን አበል በቀን ብር 383.00 በማሰብ ብር 117,920.00 ከውል ውጭ የተከፈለ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 225,010.00 (107,090.00 + 117,920.00) መንግስት ተጨማሪ ወጪ ያለአግባብ እንዲከፍል ተደርጓል፤

4. በገቢ ማመንጫ ስር የተለያዩ ሥራ ለሰሩ የቀን ሰራተኞች የተከፈለው ብር 1,935,553.10 እና ለገቢ ማመንጫ አገልግሎት ለሚዉሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች ግዢ የተከፈለው ብር 3,704,280.18 በድምሩ ብር 5,639,833.28 ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተከፈለ በመሆኑ የመደበኛ በጀት ወጪ ከፍ እንዲልና የውስጥ ገቢ ወጪ ዝቅ እንዲል አድርጎታል።
5. ዩኒቨርሲቲው በግልጽ ጨረታና በዋጋ ማቅረቢያ መግዛት ሲገባው ከመመሪያ ውጭ በድምሩ ብር 13,486,893.02 የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ቢያንስ አንድ ጊዜ ግልጽ ጨረታ ሳያወጣ በቀጥታ ግዥ የፈጸመ በመሆኑ መንግስት ከውድድር የሚያገኘውን ጥቅም እንዲያጣ አደርጎታል፡፡
6. የገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 25/07/2012 በቁጥር ማአ 30/07/45 ለገቢዎች ሚኒስቴር በፃፈዉ ደብዳቤ ለግብርና የሚዉሉ እቃዎች ከማንኛዉም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆን ማሻሻያ ያደረገ ሲሆን ዩኒቨርሲቲዉ ትራክተሮች ለመግዛት ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ አሸናፊዉ ድርጅት ኬርሜድ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር ለአንድ ትራክተር ታክስ ሳይጨምር ብር 3,608,695.00 ያቀረበ በመሆኑ የ6 ትራክተሮች ዋጋ ብር 21,652,170.00 (3,608,695.00 x 6) መከፈል ሲገባው የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ለአንድ ትራክተር ብር 4,150,000.00 ለ6 ትራክተሮች ብር 24,900,000.00 (4,150,000.00 x 6) ክፍያ በመፈጸሙ ብር 3,247,830.00 በብልጫ

ለድርጅቱ ተከፍሏል:: በብልጫ የተከፈለው ክፍያ ከድርጅቱ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል:: በተጨማሪም ድርጅቱ ያቀረበው ደረሰኝ ተጨማሪ እሴት ታክስን ያላካተተ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ክፍያውን የፈጸሙ የስራ ሀላፊዎች ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል::

7. ዩኒቨርሲቲዉ

➢ ባወጣዉ የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች ግዢ ጨረታ የቴክኒክ መመዘኛዉን ካለፉ ተጫራቾች መካከል ኑሩ ሁሴን የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ድርጅት የጎማ ኩሽነት ከነዳጆው ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ከኢክራም አብዱ ጠቅላላ የንግድ ሥራ ድርጅት በመግዛቱ ብር 507,020.00 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

➢ ለተማሪዎች ምግብ የሚውል ባለ 130 ግራም ዳቦ ለመግዛት ባወጣው ጨረታ የቴክኒክ መመዘኛዉን ካለፉ ተጫራቾች መካከል አለማየሁ አየለ የምግብ ምርቶች ድርጅት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ቢሆንም በከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ከሐምሌት አደም ዳቦና ኬክ ማምረቻ ድርጅት በመግዛቱ ብር 496,763.55 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ፤

የቴክኒክ መመዘኛውን አልፍው ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረቡ ድርጅቶች ግዢ መፈጸም ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡ ድርጅቶች ግዥ በመፈፀሙ በድምሩ ብር 1,003,783.55 መንግስት አለአግባብ ተጨማሪ ወጪ እንዲከፍል ተደርጓል፤

8. ዩኒቨርሲቲው G+4 የተማሪዎች መማሪያ ሕንፃ ለማስገንባት ከተካ ተ/ሀይማኖት የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር የግንባታ ሥራ ዉል ስምምነት የፈጸመ ሲሆን ሥራ ተቋራጩ ስራዉን በዉሉ መሰረት ባለመስራቱ አማካሪ ድርጅቱ ዩኒቨርሲቲዉ ዉል እንዲያቋርጥና ከሥራ ተቋራጩ የቅድመ ክፍያዉንና የዉል ማስከበሪያዉን እንዲወርስ ያሳሰበ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲዉ የሥራ ተቋራጩ ያስያዘውን የውል ማስከበሪያ ብር 3,554,785.30 ገቢ ያላደረገ በመሆኑ መንግስት ማግኘት የሚገባውን ገቢ እንዲያጣ አድርጎታል::

9. ለአተም ሕንፃ ሥራ ተቋራጭ በቀን 30/10/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 193677 በሂሳብ መደብ 6324 ለኤሪ ወንዝ ድልድይ ግንባታ ለብረት አቅርቦትና ሥራ በውል ከተገባው ዋጋ በላይ ብር 5,000,191.37 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤

10. በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ተማሪዎች በግቢ ዉስጥ ባልነበሩበት ከሐምሌ/2012 እስከ መስከረም/2013 ድረስ ለፌዴራል ፖሊስ አባላትና ለኮቪድ ታካሚዎች ለሚውል የምግብ

ግብዓት አቅርቦት ግዢ ብር 1,650,548.13 ወጪ የተደረገ ሲሆን የተጠቃሚዎች ዝርዝር፤ የኮቪድ ታካሚዎች በዩኒቨርሲቲው እንዲጠለሉ የተጠየቀበት ማስረጃ፤ ታካሚዎች ለምን ያህል ጊዜ በግቢ ውስጥ እንደቆዩ፤ በየጊዜው የነበሩ ታካሚዎችና የህክምና ባለሙያዎች ብዛት እና ታካሚዎቹ ከተማሪዎች በጀት እንዲጠቀሙ የተፈቀደበት ማስረጃ ለኦዲቱ ሥራ ያልቀረበ መሆኑ፤

11.በድምሩ ብር 7,949,879.87 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤

12.ከመደበኛ በጀት ብር 22,452,511.13 ለየበጀት አርእስቱ ከተደለደለው በጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ (ወጪ የተደረገ) መሆኑ እና ከመደበኛ በጀት በአንድ (1) የበጀት አርዕስት የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ብር 3,511,418.76 ወጪ የተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

## 1. <u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>

1.1 ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ አገልግሎት የሚውል እቃዎች ግዥ ሲፈፅም በግልፅ ጨረታ መግዛት ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ መግዛት ከሚቻለው ብር 200,000 እንዳይበልጥ ለማድረግ በመቆራረጥ ከተለያዩ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሣሣይ ድርጅቶችን በተደጋጋሚ በመጋበዝ በድምሩ ብር **18,028,155.41** በዋጋ ማወዳደሪያ /በፐሮፎርማ/ ተቆራርጦ ግዥ የፈፀመ በመሆኑ መንግስት ከጨረታ ግዢ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም አሳጥቶታል፡፡

1.2 ለሕንፃና ቁሳቁስ እድሳትና ጥገና የተከፈለው ብር 2,351,096.22 በ6244 (ለሕንፃ፣ ቁሳቁስ እድሳትና ጥገና ክፍያ) ሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲኖርበት በ6256 (ለአገልግሎት ክፍያ) ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤

1.3 መሠረታዊ የግዢ መስፈርቶችን ያላሟሉ ድርጅቶች ከግዢ ውድድር ውጭ መሆን ሲገባቸው የንግድ ሥራ ፈቃዳቸውን በ2013 ካላሳደሱ አቅራቢዎች እና አቅራቢዎች ከተሰማሩበት የንግድ ዘርፍ ውጭ በብር 1,835,041.66 የተለያዩ ዕቃዎች ግዢ የተፈጸመ መሆኑ፤

1.4 ዩኒቨርሲቲዉ መጋቢት 12 ቀን 2012 ዓ.ም ለተማሪዎች ምግብ ቤት የሚዉሉ የምግብ ግብዓቶችን ለመግዛት ባወጣዉ ጨረታ ለሚገዛው የእንጀራና ስጋ አቅርቦት የቴክኒክ ግምገማ የሚያስፈልግ ቢሆንም የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ሳያዘጋጅና የአቅራቢዎች አቅም ሳይገመገም በዝቅተኛ ዋጋ ላይ ብቻ በተመሰረተ የዋጋ ግምገማ የጨረታ አሸናፊዉ እንዲለይ ተደርጎ በበጀት ዓመቱ ለእንጀራ አቅርቦት ብር 9,346,254.15 እና ለስጋ አቅርቦት ብር 5,793,486.87 በድምሩ ብር 15,139,741.02 የግዥ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

1.5 የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በራሱ ኃላፊነት (ተቆጣጣሪነት) በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እየተሰሩ የሚገኙ የፕሮጀክት ሥራዎች ኃላፊነትን ለዩኒቨርሲቲው ሲያስተላልፍ በፕሮጀክት ስቶሮች ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎችን (ማቴሪያሎችን) እና ለግንባታ ሥራ ተቋራጮች የተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች (ማቴሪያሎች) በርክክብ ሰነዱ ላይ ያልተካተቱ መሆኑ፤

1.6 ለዩኒቨርሲቲው በ2013 በጀት ዓመት የተመደበለት የተስተካከለ በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው የወጪ ሂሣብ ለየበጀት አርእስቱ የተደለደለው ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 28,111,429.95 እና ከካፒታል በጀት ብር 104,193,730.64 በድምሩ ብር 132,305,160.59 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

2. **ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)**

2.1 የውስጥ ገቢ የሂሣብ እንቅስቃሴ የተመዘገበው በፌደራል መንግስት የሂሳብ አመዘጋገብ (IBEX) ሳይሆን በExcel መሆኑ፤

2.2 የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፤ አያያዝ እና አጠባበቅ በፌደራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

2.2.1 **በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት፤**

- በዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ ያልተደረጉ 1 ጀነሬተር፤ 3 የምግብ ማብሰያ ዕቃዎች እና 6 ፍሪጆች በግምጃ ቤቱ የሚገኙ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው የተመላሽ ዕቃዎች ግምጃ ቤት ያለው ቢሆንም ተመላሽ የተደረጉ 34 ላፕቶፕ፣ 7 ዴስክ ቶፕ ፣ 2 ቴሌቪዥን እና 3 ፎቶ ኮፒ ማሽን በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

2.2.2 **በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት፤**

በዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ ያልተደረጉ 1 ደርዘን የቆሎና የኩኪስ ሰሃን፣ 1 የውሃ ማሞቂያ ማሽን፣ 1 የቡና መፍጫ ማሽን፤ 2 ፊርሙዝ፣ 2 ደርዘን የሻይ ብርጭቆ እና 1 የቡና ማፍያ ማሽን በግምጃ ቤቱ የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2.3 **በተማሪዎች ክሊኒክ፤**

መድሃኒት ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ሲደረግ የመድሃኒቱ የምርት መለያ ቁጥር፣ መጠን፣ መለኪያ፣ የነጠላ ዋጋ፣ የውስጥ መለያ ኮድ እና የአገልግሎት ዘመኑን የሚገልጽ ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በገንዘብ ሚኒስቴር በሚታተም የመድሃኒት የገቢ ደረሰኝ መሰረት ገቢ የማይደረግ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2.4 **በቤተ-መጽሐፍት፤**

- የቀድሞው የቤተ-መጽሐፍት ሰራተኛ ከሥራው ሲለቅ ለተተኪው ሠራተኛ የመጽሐፍ ርክክብ ሲደረግ የመጽሐፍቱ ዓይነትና ብዛት በዝርዝር ሳይገለጽ በጥቅል መሆኑ፤
- የመጽሐፍት ግዥ ሲፈጸም የፍላጎት መጠየቂያ ከቤተ-መጽሐፍት ባለሙያ ሳይሆን ከመምህሩ እንደመነሻ ተደርጎ የመጽሐፍት ግዥ የሚፈጸም መሆኑ፤
- በቤተ-መጽሐፍት ውስጥ በርካታ የባይሎጂ መጽሐፍት የሚገኝ ቢሆንም ተጨማሪ ግዢ የተፈጸመ መሆኑ፤
- የቤተ-መጽሐፍት የዕለት ሠራተኛ ለተተኪው በሚያስረክብበት ጊዜ የርክክብ ሂደት አለመኖሩ፤
- በቤተ-መጽሐፍት ባር ኮድ ጥቅም ላይ ባለመዋሉ የሚወጡና የሚመለሱ መጽሐፍቶችን በቀላሉ ለመቆጣጠር አለመቻሉ፤
- አገልግሎት የማይሰጡ (የተበላሹ) 3 ራይዝንግ ኮፒ ማሽን፤ 2 ሪኮ ኮፒ ማሽን እና 2 ክሮሲራ ኮፒ ማሽን በቤተ-መጽሐፍት ኮፒ ክፍል የሚገኙ መሆኑ፤
- የቤተ-መጽሐፍት ሰራተኞች የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ቤተ-መጽሐፍቱ በሰለጠነ የሰው ኃይል ያልተደራጀ መሆኑ፤
- ከቤተ-መጽሐፍቱ የሚቀርቡ የግዢ ጥያቄዎች በወቅቱ ምላሽ የማያገኙ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2.5 <u>በተማሪዎች ምግብ ቤት ግምጃ ቤት፤</u>

- በተማሪዎች ምግብ ቤት የምግብ ግብዓት ርክክብ ስርዓት በመረጃ የተደገፈ አለመሆኑ፤
- የምግብ ቤት ሰራተኞች የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ምግብ ቤት የሰው ሃይል እጥረት የሚታይ መሆኑ፤
- የተማሪዎች ምግብ ቤት የምግብ ግብዓቶችን በአግባቡ ለመጠበቅ የሚያስችል በቂ ስቶር የሌለው መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው ምግብ ቤት የዳቦ መጋገርያ ማሽን የሚገኝ ቢሆንም ማሽኑ ሥራ ላይ ባለመዋሉ ዩኒቨርሲቲው የዳቦ ግዢ እየፈፀመ የሚገኝ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2.6 <u>የተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ዕቃዎችን በተመለከተ፤</u>

- መኪና ሲጠገን እና ጎማ ወጪ ሲደረግ በአዲስ የተተካው አሮጌ ዕቃ ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ብር 416,003.88 ዋጋ ያላቸው የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎችና ጎማዎች ከንብረት ክፍል ወጪ የተደረጉ ሲሆን ዕቃዎቹ ለየትኞቹ ተሽከርካሪዎች ወጪ እንደተደረጉ በዕቃ መጠየቂያውና በዕቃ ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ላይ ያልተገለጸ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

3. የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች በፌደራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መያዛቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣
   - ተሽከርካሪዎች በአንድ ሊትር ነዳጅ ይጓዛሉ ተብሎ በዩኒቨርሲቲው የቀረበው የኪሎ ሜትር ርቀት ልኬት ተወስዶ በበጀት ዓመቱ 19 ተሽከርካሪዎች በተጓዙት ኪሎ ሜትር በልኬቱ መሠረት መቀዳት የነበረበት የነዳጅ ብዛት እና የተቀዳው ነዳጅ ብዛት ሲነጻጸር ለተሽከርካሪዎቹ የተቀዳው ነዳጅ በልኬቱ ከተመለከተው ብልጫ ያለው መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

4. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በየበጀት ዓመቱ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ዩኒቨርሲቲው ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

**የ2012 በጀት ዓመት ግኝቶች፤**

- የውስጥ ገቢ እና ወጪ ሂሳብ በማኑዋል አሠራር የሚመዘገብ መሆኑና ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፤
- አቅራቢዎች በገቡት የውል ስምምነት መሠረት ባለማቅረባቸው ሳዘገዩበት ከአቅራቢዎች መሰብሰብ የነበረበት ብር 714,514.04 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- ለብር 78,405.50 የወጪ ሂሳብ የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ለውሎ አበል ብር 143,585.00 ያለአግባብ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤

**የ2011 በጀት ዓመት ግኝት፤**

- የዩኒቨርሲቲው መምህራን ከማስተማር ጫና (Over load payment) የሚያገኙትን ክፍያ ከደመወዛቸው ጋር ደምሮ መቁረጥ ሲገባው የትርፍ ሰዓቱን ክፍያ ብቻ ቆርጦ በማስቀረቱ ብር 309,856.78 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች ምግብ የሚውሉ አቅርቦቶች ግዥ ሲፈጽም በጨረታ ሰነዱ ላይ እና በውሉ ላይ የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግ ባልተገለጸበት ሁኔታ ለተለያዩ አቅራቢዎች ያለአግባብ የዋጋ ማስተካከያ (ጭማሪ) በማድረግ ብር 1,204,947.32 የተከፈለ መሆኑ፤

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳሰብን ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም።

ወርቅአፈራሁ ወንድሙ
...ትምህርት ተቋማት ኦዲት ... ዳይሬክተር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ታህሳስ 2014

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የጂንካ ዩኒቨርሲቲ

## የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

**መግቢያ፤**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የጂንካ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

**ዓላማ፤**

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤**

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በጂንካ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የጂንካ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው።

የጂንካ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. <u>የገቢ ሂሳብ</u>፣

1.1. <u>የውስጥ ገቢ ሂሳብ አመዘጋገብን በተመለከተ እና ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ የውስጥ ገቢ ሂሳብ</u>፤

1.1.1. <u>ግኝት</u>፣

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9(1) የመንግሥት መ/ቤቶች በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በተዘረጋው የሂሳብ አያያዝ መረጃ ሥርዓት በመከተል የሂሳብ ምዝገባቸውን ማከናወን እንዳለባቸው ይደነግጋል። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 8(1) ለውስጥ ገቢ ራሱን የቻለ ሂሳብ መቋቋምና እያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግሥት ሂሳብ መደብ ተለይቶ መመዝገብ እንዳለበት ይገልጻል። የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ንዑስ ቁጥር 6 (ሀ) ማናቸውም የሂሳብ እንቅስቃሴ ያላቸው ሂሳቦች ሚኒስትሩ እውቅና በሰጣቸው የገቢ እና የወጪ ደረሰኝ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ይገልፃል። (ለ) የሂሳብ እንቅስቃሴ ያላቸው ሂሳቦች በእለት መዝገብ እና በሂሳብ ሌጀር መወራረስ እንዳለባቸው ያስቀምጣል። (ሐ) በፋይናንስ ምንጫቸው የተመዘገቡ ከሂሳብ ሚዛናቸው ተወስዶ አመታዊ ሪፖርት መዘጋጀት እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል። የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- የውስጥ ገቢ የሂሣብ እንቅስቃሴ የተመዘገበው በፌደራል መንግስት የሂሳብ አመዘጋገብ (IBEX) ሳይሆን በExcel መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማር እና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች በበጀት ዓመቱ የሰበሰበው ብር 10,053,174.28 የውስጥ ገቢ እና ገቢውን ለማመንጨት ወጪ ያደረገው ብር 10,009,460.05 ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

1.1.2. <u>ስጋት</u>፣

- የመንግስት መመሪያን ተከትሎ የሂሳብ እንቅስቃሴ ምዝገባ አለማከናወን የተቋሙ አሰራር ወጥነት የጎደለው እንዲሆን ያደርጋል።
- ዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ ሂሳቡን በመመሪያው መሰረት ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት አለማድረጉ የሕግ ጥሰት ከመሆኑም ባሻገር ዩኒቨርሲቲው የሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል።

1.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት የሂሳብ አመዘጋገብ (IBEX) እንዲመዘገብ ማድረግ ይገባል። እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር የውስጥ ገቢ ሂሳቡን በየወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

1.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

የቀረበዉ ግኝት ትክክል ነዉ። በ2014 በጀት ዓመት የዉስጥ ገቢ ሂሳቦችን በIBEX ላይ ትኩረት ሰጥተን እንመዘግባል። በተሰጠን አስተያየት መሰረት ከመማር ማስተማርና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች የተሰበሰበ ገቢና ወጪ በአይቤክስ ስላልተመዘገበ ለገንዘብ ሚ/ር ሪፖርት ማቅረብ አልተቻለም። አሁን በተሰጠን አስተያየት መሰረት ከሐምሌ1/2013 ዓ/ም ጀምሮ በአይቤክስ ምዝገባ ማካሄድ ሪፖርት እናደርጋለን።

1.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

የውስጥ ገቢ ሂሳቡን በየወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በ2012 በጀት አመት ኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ምንም አይነት እርምጃ ለለመሰዱ ተረጋግጧል። በመሆኑም የስራ አመራሩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የሂሳብ ሪፖርቱ እየተዘጋጀ ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዲቀርብ በድጋሚ እናሳስባለን።

1.2. <u>ለግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ያልተከፈለ የሥራ ግብር</u>፤

1.2.1. <u>ግኝት</u>፤

በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979 በክፍል 9 አንቀጽ 97 ተቀንሶ የተያዘውን ግብር ስለመክፈል ንኡስ አንቀጽ 1 ማንኛውም ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት አካል ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ቀንሶ የሚያስቀረውን የግብር ክፍያ በ30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ መክፈል እንዳለበት ይገልጻል። የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በበጀት ዓመቱ ተማሪዎችን ላስተማሩ መምህራንና የተለያየ አገልግሎት ለሰጡ ሰራተኞች ከውስጥ ገቢ ክፍያ ሲፈፀም የተቀነሰዉ የሥራ ግብር ብር 619,180.76

ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ያልተከፈለ መሆኑ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል። ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 1 ቀርቧል።

1.2.2. ሥጋት፣

ለመንግስት መግባት ያለበት ገቢ በወቅቱ እንዳይገባ ያደርጋል። ዩኒቨርሲቲውን ባለዕዳ ያደርጋል። እንዲሁም ተጠያቂነትን ያስከትላል።

1.2.3. የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ ያልተደረገው ገንዘብ በአስቸኳይ እንዲከፈል ማድረግ ይገባል። ለወደፊቱም ሥራዎች በመንግስት መመሪያ መሰረት ሊፈጸሙ ይገባል።

1.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የቀረበዉ ግኝት ትክክል ነው፣ በD አካውንት በርቀትና ተከታታይ ት/ክፍል ከሚፈፀመው የተለያዩ አገልግሎቶች ክፍያ ላይ ተቀናንሶ የቀረው ሥራ ግብር ወደ ገቢዎች መ/ቤት ያልተላለፈ ሲሆን በ2013 ዓ/ም በጀት መዝጊያ ሰኔ30/2013 ላይ በD አካውንት የተሰበሰበ ገቢ በሙሉ ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ትሬዠሪ አካዉንት ተመላሽ ተደርጓል። በቀረበዉ ግኝት መሰረት ከሃምሌ1/2012 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/2013 ዓ/ም ድረስ ያለዉ ሥራ ግብር ተመላሽ እንዲደረግ ጥያቄ ያቀረብን ስለሆነ ገንዘቡ ሲለቀቅልን ለገቢዎች መ/ቤት ገቢ እናደርጋለን። ለ2014 በጀት ዓመትም በዚሁ አሰራር እንቀጥላለን።

2. የወጪ ሂሳብ፣

2.1. ለተማሪዎች ምረቃ ማስታወቂያ ከተገባው ውል ውጭ የተፈጸመ ክፍያ፣

2.1.1. ግኝት፣

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 (ሀ) የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ሀላፊዎች የመንግስት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ሃላፊነት እንዳለባቸው ይገልጻል። የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፣

- ጥር 15 ቀን 2013 ዓ.ም የተከናወነውን የተማሪዎች ምረቃ ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ ለሁለት ሰዓት የቀጥታ ስርጭት ለማስተላለፍ ከኢትዮጵያ ብሮድካስተንግ ኮርፖሬሽን ጋር ውል ገብቶ በባ/ወ/ማ/ቁጥር 193457 ብር 750,000.00 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን የምረቃ ስነ ስርዓቱን ለማሰራጨት ለመጡ ጋዜጠኞች ከ15/05/2013 እስከ 24/05/2013 ለቆዩበት በሚል

የ10 ቀን አበል ከብር 549.00 እስከ 724.00 በማስብ በቀን 18/06/2013 በባ/ወ/ማ/ቁ 194145 በሂሳብ መደብ 6231 ብር 107,090.00 ከውል ውጭ የተከፈለ መሆኑ፤

- ዩኒቨርሲቲው ሰኔ 26/2013 ዓ.ም የተከናወነውን የተማሪዎችን ምረቃ ሙሉ ወጪዉን ሸፍኖ ለሁለት ሰዓት የቀጥታ ስርጭት ለማስተላለፍ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር ውል ገብቶ በቀን 30/10/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 196867 ብር 1,200,000.00 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን የምረቃ ስነ ስርዓቱን ለማሰራጨት ለመጡ ጋዜጠኞች ከቀን 12/10/2013 ጀምሮ በተቋሙ ለቆዩበት የ20 ቀን አበል በቀን ብር 383.00 በማስብ ብር 117,920.00 ከውል ውጭ የተከፈለ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 225,010.00 (107,090.00 + 117,920.00) ያለአግባብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል።

### 2.1.2. ሥጋት፤

ከውል እና መመሪያ ውጭ ክፍያ መፈጸም የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ያደርጋል።

### 2.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

አላግባብ የተፈጸመው ክፍያ ለዩኒቨርሲቲው ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል። ክፍያው እንዲፈጸም ያደረጉ ሰራተኞችም መቀጣት ይኖርባቸዋል። ለወደፊቱም ክፍያዎች በመንግስት መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል።

### 2.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በሁሉም የምረቃ ዘር የመገናኛ ብዙሀን ከዩንቨርስቲው ጋር ውል በመግባት የቀጥታ ስርጭት ስራ እንዲሰሩ መደረጉ እውን ነው። ነገር ግን የዩንቨርስቲው ገጽታ ግንባታ የተሰሩ ስራዎችን በተጨማሪ ቀረጻ አድርገው እንዲሰሩና የዩንቨርስቲውን ገጽታ ለማህበረሰቡ ለማድረስ ከምረቃ ቀን በፊት በመግባት ስራዎችን በመስራታቸው ይህም ስራ በውል ውስጥ ባለመካተቱ በመሆኑ ነው።

## 2.2. ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲኖርበት አላግባብ ከመደበኛ በጀት የተፈጸመ ክፍያ፤

### 2.2.1. ግኝት፤

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 የመንግስት ሂሳብ አያያዝ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት

አደረጃጀት ስርዓት መሰረት የተፈቀደላቸውን በጀትና የወጣውን ወጪ ማሳየት እንዲችሉ ተለይቶ በተሰጡዋቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 በአንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 2 የውስጥ ገቢ ማስገኛ ስራዎች ወጪ በውስጥ ገቢ መሸፈን እንዳለበት ይገልፃል። የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በገቢ ማመንጫ ስር የተለያዩ ሥራ ለስሩ የቀን ሰራተኞች የተከፈለው ብር 1,935,553.10 እና ለገቢ ማመንጫ አገልግሎት ለሚዉሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች ግዢ የተከፈለው ብር 3,704,280.18 በድምሩ ብር 5,639,833.28 ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል። ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 2 ቀርቧል።

### 2.2.2. ሥጋት፤

ለመደበኛ ስራዎች የተፈቀደን በጀት ለሌላ ፕሮግራም ማዋል ከመመሪያ ውጭ ከመሆኑም በላይ ሥራዎች በዕቅድ እንዳይመሩ ያደርጋል።

### 2.2.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው የመንግሥት ደንብና መመሪያዎችን ጠብቆ ሥራውን ማከናወን ይኖርበታል። ለውስጥ ገቢ ስራዎች ማከናወኛ ከመደበኛ በጀት የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ ተደርጎ ለገንዘብ ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል።

### 2.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

➢ በሀብትና ልማት ገቢ ማመንጫ ዘርፍ ስር የሚያገለግሉ የቀን ምንዳ ሰራተኞች አብዛኛው ዩኒቨርስቲውን ለቀጣይ በቋሚነት የገቢ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ የመሰረተ ልማት ስራዎች እና ቋሚ ሰብሎች እንደ ቡና፤ ሙዝ ፤ፓፓያ በአጭር ግዜ ምርት ሊሰጡ የሚችሉ አይደሉም በሚደርሱበት ግዜ ግን ወጪዎችን የሚቀንሱበትና በራሳቸው ወጪዎችን የሚሸፍኑበት ሁኔታ ይኖራል። ሌሎች እንደ ጋራዥ፤የወተት ላም ቤት፤ የዶሮ ቤት ግባታዎች ዩንቨርስቲው ለመማር ማስተማር የሚያግዙ መሰረተ ልማቶች ሆነው የሚያገለግሉ እንጂ ለገቢ ማመንጫ ብቻ ታስቦ የተገነቡ አይደሉም። ስለሆነም በቀጣይ ገቢ ማመንጫ የራሱን ኢንተርፕራይዝ በሚቋቋምበት ወቅት ለብቻው ትርፍና ኪሳራውን በማስላት ወጪዎችን በራሱ የሚሸፍንበት ስርዓት በቀጣይ ለመፍጠር ከሌሎች ዩኒቨርስቲዎች ተሞክሮ በመውሰድ ላይ እንገኛለን። የተገለፀውን ስጋት በቀጣይ ለማስተካከል ከሚመለከታቸው የዩንቨርስቲው አካላት ጋር የምንነጋገርበት ይሆናል።

➢ በግኝቱ የተዘረዘሩት ግኝቶ ተፈፅሞ ስራ ላይ የዋሉ መሆኑ ሀቅ ነው። ነገር ግን የገቢ ማመንጫ ዘርፍ የሚያከናውነው ተግባር ብቻውን ትርፍ ለማግኘት ብቻ ታስቦ አይደለም። ለዩንቨርስቲው ተልኮ ደጋፊ የሆኑ ዘርፎችን በመምረጥ ለአካዳሚክ መማር ማስተማር የምርምር ስራዎችን ሊያግዙ የሚችሉ ዘርፎችን ነው እያከናወን ያለው ለዚሁም አሁን መከናወን ላይ ያሉ ስራዎች በፍጥነት ገቢ የሚያመነጩም የማያመነጩም ወደፊት የመማር ማስተማሩን እገዛ ውጤት በሚያመጣበት ወቅት ለውስጥ ገቢ ማመንጫነት ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ታሳቢ በማድረግ እየተከናወነ ነው።

## 2.3. <u>በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤</u>

### 2.3.1. <u>ግኝት፤</u>

በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5 አንቀጽ 7 በተራ ቁጥር 4 መ/ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ስርአት መሰረት የተፈቀደላቸውን በጀትና የወጣውን ወጪ ማሳየት እንዲቻል ተለይቶ በተሰጧቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል። የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለሕንፃና ቁሳቁስ እድሳትና ጥገና የተከፈለው ብር 2,351,096.22 በ6244 (ለሕንፃ፤ ቁሳቁስ እድሳትና ጥገና ክፍያ) ሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲኖርበት በ6256 (ለአገልግሎት ክፍያ) ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል። ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 3 ቀርቧል።

### 2.3.2. <u>ሥጋት፤</u>

ወጪዎች በትክክለኛው የሂሳብ መደባቸው የማይያዙ ከሆነ የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታውን ካለማሳየቱም በተጨማሪ በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

### 2.3.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

ዩኒቨርሲቲው በጀት የሚመደብለት በየወጪ ሂሳብ ርዕሱ ተለይቶ ስለሆነ የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ክፍያ መፈፀሙ መመሪያን የጣሰ ከመሆኑም በላይ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ምክንያት ስለሚሆን ለወደፊቱ ሊስተካከል ይገባል።

2.3.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የአገልግሎት ክፍያዎች ወይም የጉልበት ስራ ክፍያዎችን ቀደም ሲልም በዚህ የወጪ ሂሳብ መደብ ክፍያዎች እየፈጸምን በመሆኑ አሁን ላይ ክፍያ የተፈጸመበት የወጪ መደብ ትክክል አለመሆኑ ስለተገለጸልን በቀጣይ እናስተካክላለን።

2.4. ያለውድድር ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ የተፈጸመ ግዢ፣

2.4.1. ግኝት፣

ሰኔ 2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል። የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ከመመሪያ ውጭ ያለውድድር በቀጥታ የግዢ ዘዴ የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ተፈጽሞ ብር 13,486,893.02 የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል። ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 4 ቀርቧል።

2.4.2. ስጋት፣

ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብም ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል።

2.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ግዢዎች በግዢ መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

2.4.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- ዩኒቨርሲቲው ከመሀል ከተማ ሩቅ ቦታ ላይ የሚገኝ በመሆኑና በአጭር ጊዜ ውስጥ አወዳደሮ ስራ ለመስራት የሚያዳገት በመሆኑ አንዳንድ ግዥዎችን በቀጥታ

በማኔጅሜት በመወሰን የተገዙ ናቸው፡፡ ከዚህ በመማር አስቀድሞ በማቀድ ለመቀነስ ልምድ ወስደንበታል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው አዲስ ከመሆኑና በአካባቢው ላይ በምግብ ዝግጅት የተደራጁ ማህበራት እጥረት አንጻር ዩኒቨርስቲዉ የጅንካ ከተማ አስተዳደር አደራጅ መ/ቤትን በተጠየቀዉ መሰረት የጂንካ ከተማ አደራጅ መ/ቤት ከተለያዩ ማህበራት በመመልመል በቁጥር 60 አባላትን በላከልን መሰረት እየሰሩ የሚገኙ ናቸው፡፡

## 2.5. በዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ተከፋፍሎ የተፈጸመ ግዢ፣

### 2.5.1. ግኝት፣

ሰኔ 2002 በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀጽ 15/2 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተገለጸው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግሌጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ በአዋጁ አንቀጽ 33/4 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ አዋጁ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ሥርዓቶችን ለመሸሽ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን በመከፋፈል እንደሌለባቸው እንዲሁም፣ በመመሪያው አንቀጽ 24/1 እና 24/4 መሠረት ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋቸው በመመሪያው በተጠቀሰው መሠረት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ መፈፀም እንደሚቻል ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፣

- የግገር ፍላጎትን በማሰባሰብ ግልፅ ጨረታ በማውጣት የተለያዩ ድርጅቶችን በማሳተፍ ግገር መፈጸም ሲገባ በድምሩ የብር 18,028,155.41 ግዢ በዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) የተፈጸመ መሆኑ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 5 ቀርቧል፡፡

### 2.5.2. ሥጋት፣

ግዥ በአዋጁና መመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥም ይችላል፡፡

### 2.5.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በጥቅል ወይም በጅምላ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

### 2.5.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በዋጋ ማቅረብያ ግገር የተፈፀሙ ግዥዎች የተወሰኑት በግልፅ ጨረታ ወጥቶ በጥራትና በገንዘብ መጠን ዉድቅ የተደረገ ሆኖ በቀጣይ ግዥዎች በሌላ የግዥ ዘዴ ፈፅመናል፡፡ በቀጣይ በተቀመጠዉ መሰረት የግዥዉን ሂደት አብዛኛዉን በግልፅ ጨረታ እንፈፅማለን፡፡

## 2.6. መሠረታዊ የግዢ መስፈርት ካላሟሉ ድርጅቶች የተፈፀመ ግዢ፤

### 2.6.1. ግኝት፤

ሰኔ 2002 በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 16.19.1.2.ሀ ማንኛዉም የመንግስት መ/ቤት በጨረታዉ የተወዳደረዉ አቅራቢ መ/ቤቱ የሚፈልገዉን አነስተኛዉን የጥራት መመዘኛና ሌሎች መሠረታዊ መስፈርቶች ያላሟላ በመሆኑ ብቃት የሌለዉ ሆኖ ሲገኝ ተጫራቹን ወደ ዝርዝር ግምገማ ማሳለፍ እንደሌለበት ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- መሠረታዊ የግገር መስፈርቶችን ያላሟሉ ድርጅቶች ከግገር ውድድር ውጭ መሆን ሲገባቸው የንግድ ሥራ ፈቃዳቸውን በ2013 ካላሳደሱ አቅራቢዎች እና አቅራቢዎች ከተሰማሩበት የንግድ ዘርፍ ውጭ በብር 1,835,041.66 የተለያዩ ዕቃዎች ግገር የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 6 ቀርቧል፡፡

### 2.6.2. ሥጋት፤

ግዥዎች በመንግስት የግገር መመሪያ መሰረት የማይፈጸሙ ከሆነ ሕገወጥ አሰራርን ያስፋፋል፤ መስፈርቱን ያሟሉ ድርጅቶች እድል እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡ የመንግስት ውስን ሀብት ያለአግባብ እንዲባክን በር ሊከፍት ይችላል፡፡

### 2.6.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ግዥዎች በመንግስት የግገር መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በየጊዜው ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በግኝቱ የተጠቀሰው ግገር ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

### 2.6.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ግኝቱ ትክክል ነው፡፡ ሆኖም ከዚህ በመማር በጨረታ ጊዜ ትከረት ተሰጥቶ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

## 2.7. የቴክኒክ ግምገማ ሳይደረግ በዝቅተኛ ዋጋ ግምገማ የተፈጸመ ግዢ፤

### 2.7.1. ግኝት፤

በፌዴራል የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ቁጥር አዋጅ 649/2001 አንቀፅ 29.2 የመንግስት መ/ቤቱ ሊገዛ የሚፈለገዉን ዕቃ ጥራት፤ ጠቀሜታ፤ ተገቢ ጥንቃቄ፤ እንደ አስፈላጊነቱ መለኪያዉን፤ መለያዉን፤ መጠሪያዉን፤ አስተሻሸጉን፤ ምልክቱን ወይም የአመራረት ሂደትና ዘዴ እንዲሁም ተፈላጊ የሆነዉን ባህርይ የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበትን ሥርዐት የሚገልፅ መሆን እንዳለበት ያዛል፡፡ በ2002 የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ በአንቀፅ 17.2.ለ የሚዘጋጀዉ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የዉሉ አንድ ክፍል በመሆን የአቅርቦቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚሁ መመሪያ አንቀፅ 5.2.2.3 ተጫራች ድርጅቶች ለስራዉ ብቁ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ የአመልካቹን ቁልፍ ባለሙያዎች የሥራ ልምድ፤ የሚያስፈልግ ስራ የመፈፀም አቅም፤ ደረጃ፤ መሳሪያና ቁሳቁስ ያሟላ መሆኑ መገምገም እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በአንቀጽ 5.7.2 ለቴክኒክ ጥራት የሚሰጠዉ ክብደት ዝቅተኛ ወለል 70% መሆኑን ጠቅሶ በዚህ የመረጣ ስልት በቴክኒክ ግምገማ ከ70% በታች ያገኙ ተጫራቾች የቴክኒክ ሀሳብ ማቅረብያ ዉድቅ ይደረግና 70% እና ከዚያ በላይ ያገኙ ተጫራቾች የዋጋ መወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ መከፈት እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚሁ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ዩኒቨርሲቲዉ መጋቢት 12 ቀን 2012 ዓ.ም ለተማሪዎች ምግብ ቤት የሚዉሉ የምግብ ግብዓቶችን ለመግዛት ባወጣዉ ጨረታ ለሚገዛው የእንጀራና ስጋ አቅርቦት የቴክኒክ ግምገማ የሚያስፈልግ ቢሆንም ምንም አይነት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ሳያዘጋጅና የአቅራቢዎች አቅም ሳይገመግም በዝቅተኛ ዋጋ ላይ ብቻ በተመሰረተ የዋጋ ግምገማ የጨረታ አሸናፊዉ እንዲለይ ተደርጎ በበጀት ዓመቱ ለእንጀራ አቅርቦት ብር 9,346,254.15 እና ለስጋ አቅርቦት ብር 5,793,486.87 በድምሩ ብር 15,139,741.02 የግዥ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 7 ቀርቧል፡፡

### 2.7.2. ሥጋት፤

- ከመንግስት የግዢ መመሪያ ውጭ ግዢ መፈጸም ብልሹ አሰራርን ያበረታታል፤ የመንግስት ውስን ሀብት ያለአግባብ እንዲባክን በር ሊከፍት ይችላል፡፡

- የአቅራቢዎች የፋይናንስና የማጓጓዣ አቅም፣ የማምረቻ ቦታና ቁሳቁስ የሰራተኛ ልምድና ብዛት ሳይገመገም ግዢ መፈጸም የአቅርቦት መቆራረጥን የምርት ጥራት ጉድለት ሊያስከትል ይችላል፡፡

### 2.7.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ግዥዎች በመንግስት የግዢ መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በየጊዜው ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በግኝቱ የተጠቀሰው ግዢ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

### 2.7.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በቀጣይ የጨረታ ሰነድ ሲዘጋጅ የመመዘኛ መስፈርቱን ማቅረብ እንዳለብንና ተፈጻሚ ማድረግ አለብን፡፡ እንደሚታወቀው የአጠቃቀም ሁኔታውም መብረት፣ውሃ ፣ምግብ ማብሰያን የመሳሰሉት ከዚህ በፊትም በወጣው ጨረታ ላይ በመሆኑ በቀጣይ እነዚህን ሁሉ ታሳቢ ያደረገነ መስፈርቱን በዝርዝር ገልጸን ጨረታ ማወጣቱ ተቋሙን ተጠቃሚ ስለማድርግ ተቀብለናል፡፡

## 2.8. ለትራክተር ግዢ በብልጫ የተፈጸመ ክፍያ፤

### 2.8.1. ግኝት፣

የገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 25/07/2012 በቁጥር ማአ 30/07/45 ለገቢዎች ሚኒስቴር በፃፈው ደብዳቤ ለግብርና የሚውሉ እቃዎች ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆን ማሻሻያ ማድረጉን ገልጿል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ዩኒቨርሲቲው ትራክተሮች ለመግዛት ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ አሸናፊው ድርጅት ኬርሜድ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር ለአንድ ትራክተር ታክስ ሳይጨምር ያቀረበው ዋጋ ብር 3,608,695.00 ሲሆን ለአቅራቢው ድርጅት የ6 ትራክተሮች ዋጋ ብር 21,652,170.00 (3,608,695.00 x 6) መክፈል ሲኖርበት ዩኒቨርሲቲው የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ለአንድ ትራክተር በብር 4,150,000.00 ዋጋ ለ6 ትራክተሮች ብር 24,900,000.00 (4,150,000.00 x 6) በቀን 30/10/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 196436 በሂሳብ መደብ 6313 ክፍያ በመፈጸሙ ብር 3,247,830.00 በብልጫ ለድርጅቱ መክፈሉ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

### 2.8.2. ሥጋት፣

ከመንግስት ደንብና መመሪያ ውጭ ግዢ መፈጸም የሕግ ጥሰት ከመሆኑም በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

2.8.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

ለድርጅቱ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ተደርጎ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ድርጅቱ ያቀረበው ደረሰኝ ተጨማሪ እሴት ታክስን ያላካተተ መሆኑ እየታወቀ ክፍያው እንዲከፈል ያደረጉ የስራ ሀላፊዎች ሊጠየቁ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

2.8.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

ግኝቱ ትክክል ነዉ፡፡ ለድርጅቱ ያለ አግባብ የተከፈለዉ ገንዘብ ተመላሽ እንዲያደርጉ በ23/02/2014 በቁጥር ጂዩ/3001/14 በአድራሻ ደብዳቤ ተጽፎላቸዋል፡፡ የድርጅቱ ባለቤት ደብዳቤዉን አልቀበልም ብለዋል፡፡ ሆኖም ክስ እንዲመሰረት ለዩኒቨርስቲዉ የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ተላልፏል፡፡ በኮፒዉ ክፍልዎ እንድያዉቀዉ 1 ገጽ ደብዳቤ ተያይዟል፡፡

2.9. <u>ውል ካቋረጠ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ ያልተወረሰ (ገቢ ያልተደረገ) የውል ማስከበሪያ</u>፤

2.9.1. <u>ግኝት</u>፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 17.25.3 የመንግስት መ/ቤቱ አቅራቢዉ በዉሉ መሠረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥ በንዑስ አንቀፅ 17.25.2 መሠረት አቅራቢዉ ያስያዘዉን የዉል ማስከበሪያ ሙሉ በሙሉ መዉረስ እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚሁ መመሪያ አንቀፅ 30.1 የመንግስት መ/ቤት ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ዉሎችንና ተያያዥ ጉዳዮችን ተገቢዉን እልባት በወቅቱ አግኝተዉ ዉሉ መጠናቀቁን ማረጋገጥ እንዳለባቸዉ ይገልፃል፡፡ እንዲሁም በፊደል ተራ መ ከሶስተኛ ወገን ማለትም ከኢንተርናሽናል ኩባንያዎች፣ ከባንክና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የተያያዙ የመንግስት መ/ቤቱ ጥቅሞች መከበራቸዉንና የመንግስት መ/ቤቱ ግዴታዎች የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ዩኒቨርሲቲው G+4 የተማሪዎች መማሪያ ሕንፃ በጂንካ ከተማ ውስጥ ለማስገንባት ከተካ ተ/ሀይማኖት የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር የግንባታ ሥራ ዉል ስምምነት ፈፅሟል፡፡ ሆኖም ሥራ ተቋራጩ ስራዉን በዉሉ መሰረት አልሰራም በሚል አማካሪ ድርጅቱ ለስራ ተቋራጩ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በተደጋጋሚ የፃፈበት በሆንም የተሻሻለ ነገር ባለመኖሩ አማካሪ ድርጅቱ (አኪውት እንጂነሪንግ) በቀን 12/02/21 በደብዳቤ ቁጥር ACE/AA/JIN/002/21 ለዩኒቨርሲቲዉ በፃፈዉ ደብዳቤ ዩኒቨርሲቲዉ

ዉል እንዲያቋርጥና ከሥራ ተቋራጩ የቅድመ ክፍያዉንና የዉል ማስከበሪያዉን እንዲወርስ አሳስቧል፡፡ ዩኒቨርሲቲውም በቀን 12/06/2013 በደብዳቤ ቁጥር ጅዩ/1613/13 ለሥራ ተቋራጩ የግንባታ ሥራ ዉሉን ማቋረጡን አሳዉቋል፡፡ በዚሁ መሰረት ዩኒቨርሲቲዉ የሥራ ተቋራጩ ያስያዘውን የውል ማስከበሪያ ብር 3,554,785.30 ለዩኒቨርሲቲዉ ገቢ እንዲሆን ማድረግ ሲገባው የውል ማስከበሪያው ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.9.2. ሥጋት፤

የግንባታ ሥራ ውል ከተቋረጠባቸው ተቋራጮች የሚፈለገው የውል ማስከበሪያ ገንዘብ በውሉ መሠረት በወቅቱ ገቢ አለመደረጉ መንግሥት ማግኘት ያለበትን ጥቅም እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

2.9.3. የማሻሻያ ሃሳብ፤

የግንባታ ሥራ ውል ከተቋረጠበት ተቋራጭ የሚፈለገው የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡

2.9.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በመጀመሪያ በቀረበው ዶክሜንት መሰረት ግኝቱ ትክክል ነው፡፡ በጊዜው ዩኒቨረሲቲ ማቅረብ የነበረበት የግብዓት ዕቃዎች በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ቅውስ ምክንያት ማቅረብ ባለመቻሉ የራሱ ድርሻ የሚወስድ በመሆኑ፤ የስራ ተቋራጩ ስራውን በጊዜ መጀመር ሳይችል ቀርቶ ጊዜ መውሰዱ በተቋራጩ በኩል የሚታይ ክፍተት ቢሆንም ግንባታው የተማሪዎች የመማሪያ ክፍል በመሆኑ ክሶች ቢጀመሩ ጊዜ የሚወስድና ልናገኘው ከነበረው ገንዘብ በላይ ችግር ውስጥ ሊያስገባ እንደሚችል ከሳይስንና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የ11ዱ ፕሮጀክት አስተባባሪ ጽ/ቤት የነበራቸውን ልምድ በመቅሰም በዩኒቨርሲቲው ማኔጅሜንት ውሳኔ የፐርፎርማንስ ቦንድን ብቻ በጊዜ እንዲከፍልና ስራውን በነበረው ውል መስራት የሚችል ከዚህ በፊት የተሻለ አፈጻጸም ላስመዘገቡና ተወዳድረው በደረጃ ለተቀመጠው የስራ ተቋራጭ እንዲሰጥ በውሳኔ ያስተላለፈን መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡ ለማስረጃ የዩኒቨርሲቲው ማኔጅሜንት ውሳኔ ተያይዟል፡፡

2.9.5. የኦዲተሩ አስተያየት፤

አማካሪ ድርጅቱ ሙያውንና ክህሎቱን ተጠቅሞ ከላይ የተጠቀሰውን ምክኒያቶች በመሉ ገምገሞ ለሚያማክረው ድርጅት አዋጭ የሆነውን ሀሳብ እንደሚያቀርብ ይታመናል በመሆኑም የሥራ ተቋራጩ የግንባታ ሥራውን በገባው ውል መሠረት አለማከናወኑን

ጠቅሶ ውሉ እንዲቋረጥና ከሥራ ተቋራጩ የቅድመ ክፍያዉ እንዲሰበሰብና እና የዉል ማስከበሪያዉ ገንዘብ እንዲወርስ ያሳሰበ ቢሆንም የውል ማስከበሪያው እንዲወረስ አለመደረጉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## 2.10. ከውል ስምምነት ዋጋ በላይ ለግንባታ ሥራ በብልጫ የተፈጸመ ክፍያ፤

### 2.10.1. ግኝት፤

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤቱ ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 30/10/2013 በባ/ወ/ማ/ቁጥር 193677 በሂሳብ መደብ 6324 ለኤሪ ወንዝ ድልድይ ግንባታ ለብረት አቅርቦትና ሥራ ለአተም ሕንፃ ሥራ ተቋራጭ በውል ከተገባው ዋጋ በላይ ብር 5,000,191.37 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | የተሰራው ሥራ (የቀረበው ዕቃ) ዓይነት | የቀረበዉ ዕቃ ብዛት | ዉል የተገባበት ዋጋ | | የተከፈለው ገንዘብ | | በብልጫ የተከፈለ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ያንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ | ያንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ | |
| 1 | 83.01(a)(i) Mild steel bars (deformed Grade 40) unit. Kg | 74,044.77 | 43.32 | 3,207,619.43 | 66.83 | 4,948,411.97 | 1,740,792.54 |
| 2 | 83.01(a)(ii) High yield stress steel bars (deformed Grade 60) unit. Kg | 115,362.83 | 44.42 | 5,124,416.90 | 67.02 | 7,731,616.86 | 2,607,199.96 |
| | ድምር | | | 8,332,036.33 | | 12,680,028.83 | 4,347,992.50 |
| | | | | | | የተጨማሪ እሴት ታክስ | 652,198.87 |
| | | | | | | ጠቅላላ ድምር | 5,000,191.37 |

2.10.2. ስጋት፤

ከግገር ውል ስምምነት ውጭ ክፍያ የሚፈጸም ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

2.10.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ከውል ስምምነቱ ውጭ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ በአስቸኳይ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም ክፍያዎች በጥንቃቄ እንዲፈጸሙ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል።

2.10.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በቀረበው መረጃ መሰረት ግኝቱ ትክክል ነው። ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲው የካፒታል ፕሮጀክት በጀት ማዘዝና ማስተዳደር የጀመረው በ2013 ዓ.ም ሲሆን ውሎችን ሲያስተዳደር የነበረው የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የ11ዱ ጽ/ቤት ማስተባበሪያ ስለነበረ ዩኒቨርሲቲው በጊዜ መሬት ላይ ያለውን የግንባታ ስራዎችን ብቻ የሚከታተል በመሆኑ በውል ውስጥ የተደረጉ ለውጦችን ለማወቅ አልተቻለም። ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው ያላስተዳደረውን ውል ለማስረዳት ይቸገራል።

## 2.11. የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት የምግብ ግብዓት አቅርቦት ክፍያ፤

2.11.1. ግኝት፤

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በአንቀፅ 14.4 የመደበኛና የካፒታል የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈፀሙ ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ያዛል። የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ተማሪዎች በግቢ ውስጥ ባልነበሩበት ከሐምሌ/2012 እስከ መስከረም/2013 ድረስ ለፌዴራል ፖሊስ አባላትና ለኮቪድ ታካሚዎች ለሚውል የምግብ ግብዓት አቅርቦት ግገር ብር 1,650,548.13 ወጪ የተደረገ ሲሆን የተጠቃሚዎች ዝርዝር፤ የኮቪድ ታካሚዎች በዩኒቨርሲቲው እንዲጠለሉ የተጠየቀበት ማስረጃ፤ ታካሚዎች ለምን ያህል ጊዜ በግቢ ውስጥ እንደቆዩ፤ በየጊዜው የነበሩ ታካሚዎችና የህክምና ባለሙያዎች ብዛት እና ታካሚዎቹ ከተማሪዎች በጀት እንዲጠቀሙ የተፈቀደበት ማስረጃ ለኦዲቱ ሥራ አልቀረበም። ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 8 ቀርቧል።

2.11.2. **ሥጋት፣**

ከመንግስት ደንብና መመሪያ ውጭ ግዢ መፈጸም የሕግ ጥሰት ከመሆኑም በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

2.11.3. **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

የመንግስት ደንብና መመሪያ ማንኛውም ወጪ በተሟላ ተገቢ ማስረጃ መደገፍ ያለበት መሆኑን ስለሚያዝ ዩኒቨርሲቲው ለወጪው ተገቢ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2.11.4. **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

- የፌዴራል ፖሊስ በዩኒቨርሲቲዎች እንደቀመጡ በመንግስት የተወሰነው መሰረት በየዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ የፖለቲካና የዘረኝት አመለካከት በመስፋፋቱ ፖሊሶች በዩኒቨርሲቲዎች ወጪ ገቢ ውስጥ እንዲቆዩ በመደረጉ፤
- የኮቪድ 19 በሽታ ሲከሰት ተማሪዎች እንደወጡ የተደረገ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው የኮቪድ ማዕከል እንዲሆን የተደረገ በመሆኑ በማዕከሉ ለሚሰሩ የህክምና ባለሙያዎች እና በበሽታው ተጠርጥረው ለገቡትና ለታመሙ ዜጎች ቀለብ በዩኒቨርሲቲው እንዲሸፈን በመደረጉ ነው፡፡

2.11.5 **የኦዲተሩ አስተያየት**

ለግኝቱ የተሰጠው ምላሽ አግባብነት የሌለው በመሆኑ በማሻሻያ ሀሳቡ መሰረት ተፈጻሚ እንዲሆን እናሳስባለን፡፡

2.12. **የግንባታ ፕሮጀክቶች ሥራዎች ርክክብን በተመለከተ፤**

2.12.1. **ግኝት፣**

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች መካከል የሚፈፀም ርክክብ መመሪያ ቁጥር 10/2003 በአንቀፅ 6.3 የግንባታ ወይም የልማት ፕሮጀክቶች ሥራዎች ከአንዱ የመንግስት መ/ቤት ወደ ሌላዉ የመንግስት መ/ቤት ሲተላለፉ ርክክብ ሊደረግ እንደሚችል ይገልፃል፡፡ በዚሁ መመሪያ አንቀፅ 8.2. የተረካቢ መ/ቤት ኃላፊነት በሚለው ሥር ሀ/ መ/ቤቱን ወክሎ የርክክብ ትዕዛዝ የተሰጠባቸዉን ገንዘብ፤ ንብረትና ሰነዶች የሚረከብ ሠራተኛ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ቡድን መድቦ በጽሁፍ ለአስረካቢ መ/ቤት ያሳዉቃል፡፡ ለ/ የርክክብ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከአስረካቢዉ መ/ቤት በቀረበዉ ዝርዝር መሠረት የሚረከባቸዉ ገንዘብ፤ ንብረትና ሰነዶች በሙሉ በዝርዝር ዉስጥ መካተታቸዉን ገምግሞ ማስተካካያ የሚያስፈልገዉ ሆኖ ሲያገኘዉ እንዲስተካከል ያደርጋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በራሱ ኃላፊነት (ተቆጣጣሪነት) በዩኒቨርሲቲው ውስጥ እየተሰሩ የሚገኙ የፕሮጀክት ሥራዎች ኃላፊነትን ለዩኒቨርሲቲው ሲያስተላልፍ በፕሮጀክት ስቶሮች ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎችን (ማቴሪያሎችን) እና ለግንባታ ሥራ ተቋራጮች የተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች (ማቴሪያሎች) በርክክብ ሰነዱ ላይ ያልተካተቱ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.12.2. <u>ሥጋት</u>፣

የግንባታ ፕሮጀክት ሥራዎች ርክክብ በተሟላ ሁኔታ ካልተከናወነ የመንግስት ሀብት አላግባብ ለግለሰቦች መጠቀሚያ እንዲውል ያደርጋል፡፡ የግንባታው ሥራ ወጪ አላግባብ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

2.12.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የግንባታ ፕሮጀክቶች ሥራዎች ርክክብ በአግባቡ ተፈፅሞ እንዲስተካካል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.12.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

በወቅቱ ያልተደረገ ቢሆንም ኮንትራክተሮች የሚጠቀሙት ግብዓት ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሲላኩ በዩነቨርሲቲው ፕሮጀክት ጽ/ቤት እየተሰላ የሚሰጥ ሲሆን ትርፍ ዕቃዎች በክፍያ ጊዜ እየመለሱና ክፍያቸው እየተሰራላቸው በመሆኑ ኮንትራክተሮች ላይ የሚቀር የመንግስት ሀብት አልነበረም፡፡

## 3. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>፣

### 3.1. <u>በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>፤

#### 3.1.1. <u>ግኝት</u>፤

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ "ለ" የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ 7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበትና በንዑስ አንቀጽ "መ" ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ መመሪያው ያመለክታል፡፡ በሰኔ 30/2013 የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት መሰረት በጊዜ ገደቡ መወራረድ ሲገባው ሳይወራረድ የቆየ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

- በሂሳብ መደብ 4201 (ልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ) ብር 6,931,629.79 ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፤

- በሂሳብ መደብ 4202 (ከገንዘብ ያዥ የሚፈለግ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት) ብር 38,894.50 ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት ሳይተካ የቆየ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4211 (የግገር ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ) ብር 915,390.12 ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4273 (ከግለሰቦችና የግል ድርጅቶች የሚፈለግ ቅድሚያ ክፍያ) ብር 63,419.35 ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 4274 (ሌሎች ቅድሚያ ክፍያ) ብር 546.11 ከ1 ዓመት በላይ እስከ 5 ዓመት ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 7,949,879.87 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል። ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 9** ቀርቧል።

3.1.2. <u>ሥጋት</u>፣

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለው የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል።

3.1.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፣ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

3.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

ግኝቱ ትክክል ቢሆንም አቅራቢዎቹ ዕቃዎችን ለዩኒቨርሲቲው ሲያስረክቡ ገንዘቡ የሚሰበሰብ፣ በግሌሰቦች እጅ የሚገኝ ደግሞ በሕግ መሰረት የተያዙ ያሉ፣ ሌሎች ደግሞ በውሳኔ እንደወዳደቀ ይደረጋል።

4. <u>በጀት</u>

4.1. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>፣

4.1.1. <u>ግኝት</u>፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ

የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ በየበጀት አርዕስቱ የተመደበው የተስተካከለ በጀት እና ስራ ላይ የዋለው በጀት ሲመዛዘን ከመደበኛ በጀት ብር 28,111,429.95 እና ከካፒታል በጀት ብር 104,193,730.64 በድምሩ ብር 132,305,160.59 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት በጀት) ተገኝቷል፡፡
- በሌላ በኩል ከመደበኛ በጀት ብር 22,452,511.13 ከተፈቀደው በጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ (ወጪ የተደረገ) መሆኑ እና ከመደበኛ በጀት በአንድ (1) የበጀት አርዕስት የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ብር 3,511,418.76 ወጪ የተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 10 ቀርቧል፡፡

4.1.2. ሥጋት፤

- የተፈቀደን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ አለማዋል በበጀት ዓመቱ በዕቅድ የተያዙ ስራዎች እንዳይከናወኑ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ በሌሎች መ/ቤቶች ሊሰራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡
- እንዲሁም ከበጀት በላይ መጠቀም ደግሞ የሕግ ጥሰት በመሆኑ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

4.1.3. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሰረት በስራ ላይ እንዲያውል እና ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

➢ በጀት ያልተያዘለት ወጪ፡- ግኝቱ ትክክል ነው ወጪው የካፒታል ፕሮጀክት ወጪ ሲሆን ምዝገባ አይቤክስ ላይ ሲመዘገብ በስህተት በመደበኛ በጀት ላይ በመደበኛ የተመዘገበ በመሆኑ ነው፡፡ የሰኔ ወር ሂሳብ ሪፖርት የተዘጋና ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት የተደረገ ስለሆነ ከመደበኛ በጀት ወደ ካፒታል በጀት ወጪ ላይ

እንዲመዘገብ ለገ/ሚኒስተር በደብዳቤ በማሳወቅ የማስተካከያ ምዝገባ የሚደረግ ይሆናል።

- በመደበኛ በጀት ከበጀት በላይ ወጪ፡- በኮቪድ 19 ምክንያት ዩኒቨርስቲው ሁለት ግዜ የምርቃ ስነ ስርዓት ያካሄደ በመሆኑ የጥሬ ገንዘብ እጥረት ያጋጠመ በመሆኑ መደበኛ ላይ ከሌላ መደብ በመጠቀማችን ይህ ሊከሰት ችሏል። በመሆኑም ለወደፊቱ ጥንቃቄ በማድረግ የሚስተካከል ይሆናል።

## 5. ንብረት፤

### 5.1. የንብረት አያያዝና አመዘጋገብን በተመለከተ፤

#### 5.1.1. ግኝት፤

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. **በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት፤**
   - በዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ ያልተደረገ 1 ጀነሬተር፤ 3 የምግብ ማብሰያ ዕቃዎች እና 6 ፍሪጆች በግምጃ ቤቱ የሚገኙ መሆኑ፤
   - ዩኒቨርሲቲው የተመላሽ ዕቃዎች ግምጃ ቤት ያለው ቢሆንም ተመላሽ የተደረጉ 34 ላፕቶፕ፣ 7 ዴስክ ቶፕ ፣ 2 ቴሌቪዥን እና 3 ፎቶ ኮፒ ማሽን በቋሚ ዕቃዎች ግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

2. **በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት፤**
   - በዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ ያልተደረጉ 1 ደርዘን የቆሎና የኩኪስ ሰሃን፣ 1 የውሃ ማሞቂያ ማሽን፣ 1 የቡና መፍጫ ማሽን፤ 2 ፌርሙዝ፣ 2 ደርዘን የሻይ ብርጭቆ እና 1 የቡና ማፍያ ማሽን በግምጃ ቤቱ የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

3. **በተማሪዎች ክሊኒክ፤**
   - የፋርማሲና የላብራቶሪ ባለሙያ እጥረት የሚታይ መሆኑ፤
   - መድሃኒት ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ሲደረግ የመድሃኒቱ የምርት መለያ ቁጥር፣ መጠን፣ መለኪያ፣ የነጠላ ዋጋ፣ የውስጥ መለያ ኮድ እና የአገልግሎት ዘመኑን

የሚገልጽ ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በገንዘብ ሚኒስቴር በሚታተም የመድሃኒት የገቢ ደረሰኝ መሰረት ገቢ የማይደረግ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

4. <u>በቤተ-መጽሐፍት፤</u>

- የቀድሞው የቤተ-መጽሐፍት ሰራተኛ ከሥራው ሲለቅ ለተተኪው ሠራተኛ የመጽሐፍ ርክክብ ሲደረግ የመጽሐፍቱ ዓይነትና ብዛት በዝርዝር ሳይገለጽ በጥቅል መሆኑ፤
- የመጽሐፍት ግዥ ሲፈጸም የፍላጎት መጠየቂያ ከቤተ-መጽሐፍት ባለሙያ ሳይሆን ከመምህሩ እንደመነሻ ተደርጎ የመጽሐፍት ግዥ የሚፈጸም መሆኑ፤
- በቤተ-መጽሐፍት ውስጥ በርካታ የባይሎጂ መጽሐፍት የሚገኝ ቢሆንም ተጨማሪ ግገር የተፈጸመ መሆኑ፤
- የቤተ-መጽሐፍት የዕለት ሠራተኛ ለተተኪው በሚያስረክብበት ጊዜ የርክክብ ሂደት አለመኖሩ፤
- በቤተ-መጽሐፍት ባር ኮድ ጥቅም ላይ ባለመዋሉ የሚወጡና የሚመለሱ መጽሐፍቶን በቀላሉ ለመቆጣጠር አለመቻሉ፤
- አገልግሎት የማይሰጡ (የተበላሹ) 3 ራይዝንግ ኮፒ ማሽን፤ 2 ሪኮ ኮፒ ማሽን እና 2 ክሮሲራ ኮፒ ማሽን በቤተ-መጽሐፍት ኮፒ ክፍል የሚገኙ መሆኑ፤
- የቤተ-መጽሐፍት ሰራተኞች የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ቤተ-መጽሐፍቱ በሰለጠነ የሰው ኃይል ያልተደራጀ መሆኑ፤
- ከቤተ-መጽሐፍቱ የሚቀርቡ የግገር ጥያቄዎች በወቅቱ ምላሽ የማያገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

5. <u>በተማሪዎች ምግብ ቤት ግምጃ ቤት፤</u>

- በተማሪዎች ምግብ ቤት ስቶር የምግብ ግብዓት ገቢና ወጪ በሞ/19 ና በሞ/22 ገቢና ወጪ የሚደረገው በአንድ ሰራተኛ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ምግብ ቤት የምግብ ግብዓት ርክክብ ስርዓት በመረጃ የተደገፈ አለመሆኑ፤
- የምግብ ቤት ሰራተኞች የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ምግብ ቤት የሰው ሃይል እጥረት የሚታይ መሆኑ፤

- የተማሪዎች ምግብ ቤት የምግብ ግብዓቶችን በአግባቡ ለመጠበቅ የሚያስችል በቂ ስቶር የሌለው መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው ምግብ ቤት የዳቦ መጋገርያ ማሽን የሚገኝ ቢሆንም ማሽኑ ሥራ ላይ ባለመዋሉ ዩኒቨርሲቲዉ የዳቦ ግዢ እየፈፀመ የሚገኝ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

6. <u>የተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ዕቃዎችን በተመለከተ፤</u>

- መኪና ሲጠገን እና ጎማ ወጪ ሲደረግ በአዲስ የተተካዉ አሮጌ ዕቃ ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ ስመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ብር 416,003.88 ዋጋ ያላቸው የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎችና ጎማዎች ከንብረት ክፍል ወጪ የተደረጉ ሲሆን ዕቃዎቹ ለየትኞቹ ተሽከርካሪዎች ወጪ እንደተደረጉ በዕቃ መጠየቂያውና በዕቃ ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ላይ ያልተገለጸ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል። ዝርዝሩ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

| ተ.ቁ | ቀን | የሞዴል 22 ቁጥር | ወጪ የተደረገለት መኪና የሰሌዳ ቁጥር | ወጪ ያደረገዉ ሾፌር ስም | የዕቃዉ አይነት | የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 16/09/13 | 0707281 | አልተገለጸም | ተመስገን አንጀሎ | ፕሮሰኖ ሽራና ኩሽኔት | 24,433.19 |
| 2 | 18/09/13 | 0707282 | ›› | ሰድራቅ ማምሬ | ብሪጅስቶን ጎማ | 212,608.75 |
| 3 | 11/10/13 | 0707287 | ›› | ተስፋዬ ጌታቸው | ብሪጅስቶን ጎማ | 57,000.00 |
| 4 | 17/10/13 | 0707293 | ›› | ታጋይ ጨነቀ | የፊትና የኃላ አሞርዛተር፤ የፊትና የኂላ ፍሬን ሸራ | 121,961.94 |
| | | | | | ድምር | 416,003.88 |

5.1.2. <u>ሥጋት፤</u>

የተጠቀሱት በንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የሚታዩ ግድፈቶች ለመንግስት ንብረት መጥፋትና መጉደል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

5.1.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዲስተካከሉ አፋጣኝ ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

5.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

1. <u>የቋሚ ዕቃዎች ስቶርን በተመለከተ የተሰጠ ምላሽ፤</u>
   - ጀነሬተሩ ገቢ ያልተደረገው በአደራ የተቀመጠ ስለሆነ የህንጻ ርክክብ ሲደረግ የሚወሰን ይሆናል፡፡
   - ፍሪጅና የማብሰያ እቃዎች ገቢን በተመለከተ መጋቢት 2012 ኮቪድ 19 ምክንያት ግለሰቡ አምጥቶ እስካሁን ስልኩም ሆነ አድራሻው ያልተወቀ ስለሆነ ንብረት አሁን ላይ ተወስኖ ወደ ተግባር እንዲውል ይደረጋል::
   - ተመላሽ እቃዎችን ኤሌክትሮንክ ከዋናዉ ስቶር ወደ ታች ለመውሰድ ከዚህ በፊት የአንድ ሁኔታም አስተማማኝ ባለመሆኑ ለግዜው በዋናው ስቶር አስቀምጠናል ከዚህ በኃላ አየተጠና ስለሆነ እንለያለን::
2. <u>የቋሚ ዕቃዎች ስቶርን በተመለከተ የተሰጠ ምላሽ፤</u>
   - የጥራት ኮሚቴ በሳምንት ሁለት ቀን ስለሚመለከቱ የጥራቱ ሁኔታ እለክታይ ድረስ ለብቻ የተቀመጠ ሲሆን ለወደፊት ጊዛዊ ማቆያ ስለዘጋጀ እነዚህ ችግሮች ይቀረፋሉ፡፡
3. <u>የተማሪዎች ክሊኒክን በተመለከተ የተሰጠ ምላሽ፤</u>
   - የፋርማሲና የላብራቶሪ ባለሙያ ያለመሟላት ጉዳይ በተደጋጋሚ የሰው ሀይል እንዲቀጠር የተጠየቀ ቢሆንም ገበያ ላይ የባለሙያ እጥረት ምክንያት ሊሟላ ባለመቻሉ ነው፡፡ ነገር ግን የ2014 ዓ.ም እቅድ መሰረት ጥያቄ አቅርበናል::
   - የመድሀኒት ገቢ ሞዴል የተለያየበት ከዚህ በፊት ግንዛቤው ባለመኖሩ ስንሰራ መቆየቱ ቢታወቅምን አሁን ግን በተሰጠን አስተያየት የመድሀኒት ሞዴል ለብቻ መታተም እንዳለበት ከዚህ በኃላ እናስተካክላለን::
4. <u>ቤተ-መጽሐፍትን በተመለከተ የተሰጠ ምላሽ፤</u>
   - ቤተ መጻሐፍት ርክብክብን በተመለከተ ገና ጠቅላላ ቆጠራ ብቻ የተዳረገ መሆኑን ለማስረከብ በዝርዝር ገና እያታያ መሆኑን እንገልጻለን፡፡
   - የቤተ መጻሐፍት ግገር ጋር ተያይዞ የተመለከተው ሃሳብ ትክክል ነው፡፡
   - መገዛት ያለበት መጻሐፍ እያለ አላስፈለጊ መጻሐፍ የሚገዛበት ምክንያት ባለቤቱ በተገቢ ባለመሳተፋ መሆኑን ትክክለኛ መረጃ ነው፡፡
   - የዕለት ርክብክብ በተመለከተ የተቀመጠው አስተያየት ተቀብለናል፡፡
   - የቤተ መጻሐፍት ሠራተኛ በቂ ስልጠና አላማገኛቱቸው ትክክል ነው፡፡

